# ከቤንቺ ማጂ በገኘው ፓርቲ የተፈናቀሉ ዜጎች አዳስ አበባ መግባት ጀመሩ፡፡

## ተፈናቃዮቹ በመኢአድ ዋናው ጽ/ቤት ግቢ ወስጥ ሠፍረዋል፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ በቤንቺ ማጂ ዞን በጉራ ፋርዳ ወረዳ የሚኖሩ የአማራ ክልል ተወላጆች ለብዙ ዓመታት ከኖሩበት ቀዬ ባስቸኳይ ለቀው እንዲወጡ በክልሉ ማግሥት ተጽዕኖ የተደረገባቸው በመሆኑ ወደ አዳስ አበባ መፍለስ ጀምሪዋል፡፡ አዳስ አበባ መግባት የጀመሩት ማጋቢት 13/2004 ዓ.ም. ሲሆን እንደመጡ ወደ ቅደስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን የሄዱ ቢሆንም በዚያ እንዲቆዩ ያልተፈቀደላቸው በመሆናቸው የመላው ኢትዮጵያ አንደነት ድርጅት (መኢአድ) በዋናው ጽ/ቤት ግቢ ወስጥ እንዲያርፉ አደርጓቸዋል፡፡ በዕለቱ ሰባ ያህል (70) ያህል ሰዎች ወደ አዳስ አበባ የመጡ ሲሆን ሌሎች በርካቶችም በማገድ ላይ መሆናቸውን ቀድመው የደረሱ ተፈናቃዮች ይናገራሉ፡፡




ተፈናቃዮቹ በከፊል /በመኢአድ ጽ/ ቤት ወስጥ/

ከዚህ በፊትም የካቲት 27/2004 ዓ.ም ከቤንቺ ማጂ ዞን ከጉራ ፋርዳ ወረዳ 50 ሰዎች ሜሬታቸውን ተነጥቀው ከተባረሩ በኋላ አዳስ አበባ መጥተው የነበረ ሲሆን በወቅቱ በፌደራል ፖለስ ተይዘው በአራዳ ክፍለ ከተማ አዳራሽ ወስጥ ለአራት ቀናት ካቆዩዋቸው በኋላ በኃይል ወደ ቤንቺ ማጂ ዞን ተወስደው ለአስራ አንድ ቀን ታስረዋል፡፡ ከእነዚህ ወስጥ የተወሰኑት በትናንቱ ዕለት በድጋሚ አዳስ አበባ ገብተዋል፡፡

በአሁን ወቅት ከሚኖሩበት ሥፍራ እየተደበደቡ፣ እየታሠሩና እየተሰደቡ እንዲወጡ የሚደረጉት ዜጎች ከሰሜኑ የአማራ ክልል ተነስተው ኑሮዋቸውን በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በቤንቺ ማጂ ዞን በጉራ ፋርዳ ወረዳ አደርገው ከ12 ዓመት በላይ በህጋዊ መንገድ በይዞታቸው ሥር ላለው ሜሬት ግብር እየከፈሉ በመኖር ላይ የሚገኙ መሆናቸው ይታወቃል፡፡



ሴቶችና ወንዶች ልጆች በከፊል

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ያነጋገራቸው እነዚህ ተፈናቃዮች በአካባቢው ሄደው እንዴት መኖር እንደጀመሩ ሰናገሩ <<ወደአካባቢው እንደሄድን የአገር ሽማግሌዎችና የቀበሌ ኃላፊዎች ሰንበሌጥ ያለበትን ቦታ ለመኖሪያና ለእርሻ ሰጥተውን ሰንበሌጡ ማጥረን ቤት በማሠራት እርሻ እያረስን መኖር ጀመርን፡፡ አገሩ መንገድ ስላልነበረው መኪና አይገባም ነበርና ለሁለት ዓመት ያህል በእጃችን ቆፍረንና ደልደለን 17 ከሎሜትር ርዝመት ያለው የመኪና መንገድ ሠራን፡፡ ኃላፊዎቹ ለሜታችንም ህጋዊ የሜት ባለቤትነት ሰነድ ሰጡን፡፡ የግብርና ባለሙያም ተመድቦልን ጥሩ እንድናመርት ያማክረን ጀመር፡፡ ካቢኔዎች እየመጡም በርቱና ሥሩ አገሩም ይለወጣል፤ እናንተም ታድጋላችሁ፡፡ እያሉያ ያበረታቱን ነበር፡፡ በእርሻ ሜታችንም ላይ መኩ፣ ሽንኮራ፣ ማንጎ፣ ቡና፣ አቡካዶ፣ ሩዝና ሌሎችንም ፍራፍረና ሰብሎች በጥሩ ሁኔታ ማምረት ጀመርን፡፡ ለልጆቻችን መማሪያም ትምህርት ትቤትም ሠራን፡፡





አባወራዎቹበከፊል

<<ነገርግን ነሃሴ 2003 ዓ.ም. መሬት መለካት መጣ እና መሬታችሁ ባንክ ገብቷል፤ የመሬት ባለቤት አይደላችሁም ተባልን፡፡ ከጥር 30/2004 ዓ.ም.ጀምሮ አካባቢውን ለቃችሁ ትወጣላችሁ ተባልን፡፡ የወረዳው ካቢኔ ኃላፊ አቶ አበበ ሻሜ የወረዳውን የፖሊስ አዛዥ አቶ ምክርንና 12 ፖሊሶች ይዘው መጥተው <<መሬታችንን ወደን፣ ፈቅደን ለቀናል>> እያላችሁ ፈርሙ አሉን፤ እኛም አንፈርምም አልን፡፡ እንግዲህ ያን ጊዜ ጀምሮ ነው ሹማምንቱ እኛን ቁም ስቅል ማየት የጀመሩት፡፡ 27 ሰዎች አፈሙዝ ተደግኖብን መሬታችንን ፈቅደን ለቀናል ብላችሁ ፈርሙ ተብለን ፈረምን፡፡ ቤታችንንም የእናንተን ቆርቆሮ የማዛ የለም ብትፈልጉ አቃጥሉት ተባልን፡፡ አንፈርምም ስንል ድብደባውና እስራቱን እያፀኑብን መጡ፡፡ አራት ተወካዮች መርጠን ወደ ወረዳ አመራሮች ላክን፤ ተወካዮቻችን አንቀበላችሁም፤ አናውቃችሁም፤ ዜጎች አይደላችሁም ተባሉ፡፡ ተወካዮቻችን ዞንም ሄዱ ዞንም አንቀላችሁም አላቸው፡፡ አዋሳ የክልሉ ፕሬዚዳንት የአቶ ሽፈራው ሽገጤን ተወካይ አቶፋሲካን አነጋገሩ፤ እሳቸውም የክልሉ ምክርቤት የወሰነው በመሆኑ አካባቢውን ለቃችሁ ወጡ አሏቸው፡፡

አዲስ አበባም ተወካዮ ችምክር ቤት፣ እንባጠባቂ ፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ሄደን አቤት አልን፡፡ ምንም ለውጥ አልመጣም፡፡ በአካባቢያችን ያሉት ሹሞች በዱላና በጫማ ጥፊ ይቀጠቅጡናል፡፡ በእስር ቤት ያንገላቱናል፡፡ አራሶች እና ነፍሰጡሮች ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው ቤት ለቤት በማሽሉክሉክ ላይ ናቸው፡ ፡ ይኸው እንደምታዩት ህፃን ልጆቻችንም




ጥቂቶች በእንቅልፍ ላይ ሆነው

ከእኛው ጋር ተሰደዋል፡፡ የ1,000.00 ብር ሩዝ በ200.00 ብር፣ የ6,000.00 ብር በሬ በ2,000.00 ብር ለመሸጥ ተገደናል፡፡ የምናደርገው ግራ ግብት ብሎናል፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ በደል የሚደርሱብን ሹማምንቶቹ እንጂ ህዝቡ አይደለም፤ ከህዝቡ ጋር አሁንም ሰላም ነን፤ እዚያ በነበርን ጊዜ እኛ ጋ በዓል ሲኖር እቤታችን መጥተው አብረን እናከብራለን፡፡ የእነሱንም በዓል እንዲሁ በጋራ ስናከብር ቆይተናል፡፡ ሟር ሲቆርጡ አምጥተው ይሰጡናል፡፡ አሁን እኛ ወጡ ስንባል የሸኙን በእንባ እየታጠቡ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ዕቃዎቻችንን እነሱ ጋ አስቀምጠን ነው የወጣነው፡፡>> በማለት በተሰበረ ልብ የደረሰባቸውን አጫውተውናል፡፡

አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች ህዝቡ በዘር ሳይከፋፈል እርስ በርሱ ተዋዶና ተከባብሮ እንደሚኖርና ነገር ግን የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ያለው መንግሥት አገልጋዮች ህዝቡን ለማጣጣል የሚያደርጉት ሴራ ያመጣው ችግር መሆኑን ይናገራሉ፡፡ አስተያየት ሰጭዎቹ ልማዊ ነኝ እያለ ዘወትር ጠዋትና ማታ የሚናገር መንግሥት አካባቢውን አልምተው ጥሩ ደረጃ ያደረሱ ገበሬዎችን ከቦታቸው ሚያናቀሉ በተግባር ከሚናገረው በተቃራኒ ያለ መሆኑን ያሳያል ይላሉ፡፡



ተፈናቃዮቹ ከቀያቸው ይዘዋቸው የወጡ ዕቃዎቻቸው - በማኅአድ ግቢ ወስጥ

አሁን በማኅአድ ግቢ ከሠፈሩት ወስጥ ህፃናትና እናቶች በቁጥር ይበዛሉ፡፡ በወባ፣ በታይፎይድና በአለርጂ በሽታ እየተሰቃዩ ያሉ ተፈናቃዮችም ተኝተው ይታያሉ፡፡ አንዳንድ አባወራዎች እንዳይታሰሩ ሰግተው ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን እዚያው ቤንቺ ማጂ ትተዋቸው ወደ አዳስ አበባ የማጡ መሆናቸውንም ይገልፃሉ፡፡



፡

በከፊል የተኙ ህፃናት

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የችግሩን አስከፊነት ተገንዝቦ መፍትሔ እንዳፈለግ ለደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት፣ ለፌደሬሽን ምክር ቤትና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ደብዳቤ መጻፉ ይታወቃል፡፡




ልጆችና አባወራዎች በከፊል

መኢአድ የእነ ዚህ ዜጎች ከቦታ ቦታ ተዘዋወሮ የመኖር፣ የመሥራትና ሃብት የማፍራት መብታቸው እንዲከበርላቸው አጥብቆ ጠይቋል፡፡ ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎችም ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ሰጥቷል፡፡ በወጭ ሃገር የሚገኙ የመኢአድ ድጋፍ ሠጭ ማኅበሮችም ለካናዳ መንግሥት፣ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለባራክ ኦባማና ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሃፊ ለባንኪሙን ጉዳዩ መፍትሄ እንዲፈለግለት ደብዳቤ አስገብተዋል፡፡




አንድ አባወራና ህፃናቱ በከፊል






ስደተኛው ህፃን ከባዶ ሣህን ጋር ሲታገል

መኢአድ አሁንም የምግብ፣ የመድሃኒትና የማጠለያ ድጋፍ የሚፈልጉትን እነዚህን በግፍ ከቀያቸው እንዲወጡ የተደረጉትን ዜጎች የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች፣ በጎአድራጊዎችና ሌሎችም ግለሰቦች እና ተቋማት እንዲጎበኟቸው ጥሪወን ያስተላልፋል፡፡